በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Federal Democratic Republic of Ethiopia
CIVIL SERVICE COMMISSION

ቁጥር/Ref.No ሲሰኮ/ኮቢ/486/14

ቀን/ Date 06 ጥር 2014

በዝርዝሩ ለተመለከቱት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በሙሉ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>በመንግሥት ሠራተኞች የድልድል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 859/2014 ላይ ተጨማሪ ውሳኔዎችን ስለማስተላለፍ</u>

የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤቶች መዋቅራዊ አደረጃጀት ለውጥ መሠረት የመንግስት ሠራተኞች የድልድል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 859/2014 ከኮሚሽናችን ህዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር ሲሰኮ/ኮቢ/463/14 በተጻፈ ደብዳቤ መተላለፉ ይታወሳል፡፡

መስሪያ ቤቶች ወደ አፈጻጸም ሲገቡ የ5ኛ ዙር የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የነበሩና የአገልግሎት ዘመናቸውን አጠናቀው በኮሚሽናችን በኩል በፌዴራል መስሪያ ቤቶች ምደባ የተሰጣቸው አባላት በምክር ቤቱ ቆይታቸው የስራ አፈጻጸም ምዘና የማይሞላ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለሆነም በድልድል መመሪያው ለስራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት የተቀመጠውን መስፈርት በተመለከተ እና ለባለሞያዎች የስራ መደብ የፈተና ውጤት በመስፈርትነት ያልተካተተ በመሆኑ እንደ የመስሪያ ቤቶቹ ፍላጎት ፈተና የሚሰጥበት ሁኔታ እንዲኖር በኮሚሽናችን በኩል ውሳኔ እንዲሰጥበት ከተለያዩ ተቋማትም ጥያቄ ቀርቧል፡፡

በመሆኑም በመመሪያው ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲገጥሙ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እየቀረበ ውሳኔ የሚሰጥበት ስለመሆኑ በድልድል መመሪያው የተደነገገ በመሆኑ በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት ተጨማሪ ሰርኩላር ማስተላለፍ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

(ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር



ስልክ /Tel +251115 54 96 66/67
ፋክስ /Fax +251 115 54 97 07
Email:- ethiocsc@gmail.com
Website:- www.csc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa Ethiopia

ማገልገል ክብር ነው! ድህነትን ለማሸነፍ ማገልገል ደግሞ ድርብ ክብር ነው!
Serving to Beat Poverty is Double Honor!

በዚህም መሠረት፡-

1. በየመሥሪያ ቤቱ የተመደቡ የምክር ቤት አባላት ለቡድን መሪ፣ ለዴስክ ኃላፊ፣ ለስራ አስፈጻሚ፣ ለመሪ ሥራ አስፈፃሚ፣ ለዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ለጽ/ቤት ኃላፊ ላሉ የኃላፊነት የስራ መደቦች ላይ በድልድሉ ሲወዳደሩ ለስራ አፈጻጸም የተሰጠው 10% እና ለፈተና ውጤት የተሰጠው 15% ቀሪ ሆኖ በሌሎቹ መስፈርቶች ላይ ተጨምሮ ማለትም ለትምህርት ዝግጅት 25% የነበረው 40%፣ ለሥራ ልምድ 15% የነበረው 25% ሆኖ እንዲወዳደሩ፣
2. በየመስሪያ ቤቱ የተመደቡ የምክር ቤት አባላት ለአማካሪ እና ከቡድን መሪ በታች ላሉ የባለሞያ ወይም ሰራተኛ የስራ መደቦች ላይ በድልድሉ ሲወዳደሩ ለስራ አፈጻጸም የተሰጠው 30% ቀሪ ሆኖ በሌሎቹ መስፈርቶች ላይ ተጨምሮ ማለትም ለትምህርት ዝግጅት 40% የነበረው 55% ሆኖ እና ለስራ ልምድ 30% የነበረው 45% ሆኖ እንዲወዳደሩ፣
3. ለአማካሪ እና ከቡድን መሪ በታች ላሉ የባለሞያ ወይም ሰራተኛ የስራ መደቦች ላይ ለሚወዳደሩ የፈተና ውጤትን በመስፈርትነት መጠቀም የሚፈልጉ መስሪያ ቤቶች ለትምህርት ዝግጅት የተሰጠውን 40% ለፈተና ውጤት በመጠቀም እና ቀሪዎቹን መስፈርቶች እንዳለ በመውሰድ እንዲወዳደሩ፣

እንዲደረግ የተወሰነ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

[signature]

...ሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)

ኮሚሽነር

ግልባጭ

- ለኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለሰው ሀብት ህጎች ጥናትና ኦዲት ዳይሬክተር ጄኔራል
- ለሰው ሀብት ህጎች ጥናትና ስርፀት ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ኦዲት ዳይሬክቶሬት

ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

ለከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር

ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

ለማዕድን ሚኒስቴር

ለባህልና ስፖርት ሚኒስቴር

ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ለጤና ሚኒስቴር

ለቱሪዝም ሚኒስቴር

ለፍትህ ሚኒስቴር

ለግብርና ሚኒስቴር

ለትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር

ለትምህርት ሚኒስቴር

ለገንዘብ ሚኒስቴር

ለውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር

ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

ለሰላም ሚኒስቴር

ለመስኖና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር

ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር

ለሥራና ክህሎት ሚኒስቴር

ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር